# ልዩ ጥንቅር

## ምሥራቅ ወለጋ

# የአማራው ሕዝብ ዕልቂት በአንድ ዘር ላይ የተነጣጠረ ጥቃት

ኦርዮን

የጉሣ ግጭትና የሕዝብ ዕልቂት፣ ዛሬ ዛሬ፣ ጆሮአችን፣ እንዲያም ሲል ዓይናችን እየለመደው መጣና እንደ ሌላው ጊዜ ብዙም የሚሰቀጥጥና የሚዘገንን ወሬ አይደለም። ዛሬ ከአለንበት ጊዜ ላይ የደረስነው ባለፉት ዓሥር ዓመታት የበደኖን፣ የአርባ ጉጉን፣ የአርሲን፣ የአደባባይ ኢየሱስን፣ የጌዴኦንና የጉጂን፣ ወዘተ፣ ግጭትና ዕልቂት እየሰማንና እያየን ነው። የመከራ ጊዜ ረዥምም ነው ይባላል። ግን ደግሞ ከዚያም በላይ ዓሥር ዓመት ራሱ አጭር ጊዜ አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሞትና ከዕልቂት፣ ከስደትና ከፍርሃት ጋር መኖሩን በግዱ እየተላመደው ነው ማለት ይቻላል። ዛሬ ኢትዮጵያ ላይ ሌላው ቀርቶ ለሰልፍ የወጣን ተማሪ፣ ለምርጫ የተነሳን ሕዝብ፣ በጥይት መደብደብና በቦምብ መጨፍጨፍ አዲስ ነገር እየሆነ አይደለም። ሞትንና ዕልቂትን ሁሉም ከልጅ እስከ አዋቂ እየቀመሰው ነው። «ሞት ይለመዳል? ዕልቂት ይለመዳል?» ብሎ መጠየቅ ሌላ ነገር ነው። ሀቁ ግን ከሞትና ከዕልቂት ጋር እየኖርን ነው። ቡሬ ላይ በቆየሁባቸው ጥቂት ቀናት የተረዳሁት ይህንን ሀቅ ነው።

ብዙዉ ሰው እንዲሁ በተለምዶና ለአፉ ብቻ ካልሆነ በስተቀር ዛሬ «ግጭቱን ማን ፈጠረው? ግድያውን ማን ፈጸመው?» ብሎ መጠየቁን ትቷል። የትም ይሁን የት፣ በጉሣዎች መካከል የሚቀጣጠለው ኹከትና ግጭት በእነማን ፍላጎትና በእነማን ግፊት እንደሚካሄድ ልቡ ያውቀዋል። ለሰልፍ የሚወጡ ልጆች፣ ለምርጫና ለመብት ጥያቄ የሚነሳው ሕዝብ በእነማን ታጣቂዎች፣ በእነማን ጠበንጃና ጥይት እንደሚወድቅ ሁሉም ያውቃል።


በዚህ ምክንያት፣ የዛሬውን የአገራችንን ሁኔታ በውል ለምታውቁ አንባብያን ሁሉ በዚህ ልዩ ጥንቅር ውስጥ የምናቀርብላችሁ ታሪክ ምን ያህል አዲስ ሊሆንባችሁ እንደሚችል አናውቅም። ብቻ በዚያም በሉት በዚህ፣ አንድ ነገር ማረጋገጥ ይቻላል። በምሥራቅ ወለጋ በአንድ ዘር ላይ ተነጣጥሮ የተካሄደውን የጭፍጨፋና የዕልቂት ታሪክ ስታነቡ ከግምትና ከአጠቃላይ እምነት ውጭ የዚህ ጭፍጨፋና ዕልቂት ባለቤት፣ እጅ ከፍንጅ ሲያዝ ታዩታላችሁ። ከዕልቂቱና ከሰቆቃው ተርፎ ጉጃም ውስጥ፣ ቡሬ ከሚባል ከተማ ላይ የሰፈረው የጉጃምና የጉንደር፣ የሸዋና የወሎ አማራ በእንባውና በደሙ ይናገራል። ስሙት።

## ቡሬ ሠፈራ ጣቢያ

መጋቢት 15 ቀን፣ ሐሙስ፣ ከማርቆስ ተነስቼ 10 ሰዓት ገደማ ቡሬ ደረስሁ። ጓዜን ከአንድ ቦታ አስቀምጬ ወዲያው ወደከተማ ወጣሁ። ብቻየን ነኝ። ቡሬን ብዙ አላውቃትም። የከተማው ዋና መንገድ ቡሬን ለሁለት ገምሷት ያልፋል። አብዛኛው የከተማው ክፍል ከመንገድ በላይ ዳገታማውን ሥፍራ ይዟል። ቀሪው ከተማ ከመንገዱ በታች ቁልቁል ከሚታይ ረባዳ ቦታ ላይ ይገኛል።

«ሠፋሪዎቹ የት ነው ያሉት?» ብዬ መጠየቅ አላስፈለገኝም። ከአውራው ጉዳና ዳር ቆሜ ሳማትር ከወደ ረባዳው የከተማው ክፍል፣ በብዙ ሁኔታ ተመሳሳይ የሆኑ ሰዎች አንዲት መንገድ ይዘው ሲመላለሱ አየሁ። ወደ መሐል ከተማው ይመጣሉ። በዚያው መንገድ ወደመጡበት ይመለሳሉ። ሕፃናት ልጆች ያዘሉ እናቶች፣ ሕፃናት ልጆችን የተሸከሙ ወይም እጆቻቸውን ይዘው የሚጎትቱ አባቶች፣ ዕድሜአቸው የገፋ ባልቴቶችና ሽማግሌዎች በዚያ መንገድ ይመላለሳሉ። «እነዚህ ሠፋሪዎች ናቸው» አልሁ። ጊዜው እየመሸ ነበርና አንዱን ቀረብ ብየ ለማነጋገር ወሰንሁ። አንድ ሕፃን ደረቱ ላይ አቅፎ የያዘ ጎልማሳ አየሁና ሄድሁ።

✸ ጠጋ ብዬ «ሠፋሪ መሰልኸኝ፤» አልሁት።
➲ «አዎን ሠፋሪ ነኝ፤» አለኝ።
✸ «ምን ፍለጋ ቆመሃል?»
➲ «ሥራ የሠራሁለት ሰው ነበረ። ገንዘብ እዚህ ድረስ አመጣልሃለሁ ብሎኝ እሱን እየጠበቅሁ ነው።»
✸ «መሽቷል። ከእንግዴህ ይመጣልሃል?»
➲ «እሱስ መሽቷል። ከእንግዲህ እንኳን አይመጣም። የሰው ነገር።» አለና ለመሄድ ፊቱን አዞረ።



አዲሱ

✸ ቶሎ ብየ «ወደዚህ እንሂድና እህል እንቅመስ» አልሁት። አንገቱን ሰበር አድርጎ «እሺ» አለ። አጠገባችን ከምትገኝ ጠላ ቤት ገባን። ምግብም አለ። እንጀራ በወጥ፣ ከጠላ ጋር ቀረበልንና በላን። ጠጣን። እየመሸ ስለሆነ ሰውየው ወደ ሠፈራ ጣቢያው ለመመለስ ልቡ ቆሟል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ፦

✸ «ይኸ ሕፃን የአንተ ልጅ ነው?» አልሁት።
➲ «እህስያ። የኔ ነው እንጂ።»
✸ «እናቱስ?»
➲ «እናቱንማ በጥይት ገደሉብኝ።»
✸ «ሴቷን ልጅ?»
➲ «አዎን። ምን ምርጫ አለ። ሴቱን፣ ሕጣኑን፣ ሽማግሌውንና ባልቴቱን አይደል የፈጁት። መቸ መረጡ። እና ይኸው ጨቅላ ልጅ ታቅፌ ቀረሁ።» እያለ ሕፃኑን እንደታቀፈ ለመኑሳት ሽመሉን ከጉኑ ሳበ።
✸ «ስንት ዓመቱ ነው?»
➲ የልጁን ዓይን እያየ «ቀረብህ? ሁለት ዓመቱ ነው። እናቱ ጥላው ስትሞት ጊዜ ቀረብህ አልሁት» እያለኝ ከቤት ወጣን። ከመለያየታችን በፊት ስለ ሠፈራው ጠየቅሁት።
✸ «የሠፈራው ቦታ ከዚህ ይርቃል?»
➲ አቅጣጫውን በአገጩ እያመለከተ «ኧረ እዚህ ነው፤ ቅርብ አይደል?» አለኝ።
✸ «እናንተ እንደልብ እየወጣችሁና እየገባችሁ መሰለኝ። ሌላስ ሰው መግባትና መውጣት ይችላል?»
➲ «ምን ችግር አለዋ! ይኸው እንደሚያዩት እኛም ስንመላለስ እንውላለን። ሌላውም ሰው ከልካይ የለውም። ይመጣል። ይሄዳል፤» አለኝ። «ደህና እደር» ተባብለን ተለያየን። በሁለት እጁ ቀረብህን ደረቱ ላይ ጥብቅ አድርጐ ይዞ በቁልቁለቱ ደፋ ደፋ እያለ ሄደ።

ሠፈራው ቅርብ ነው። «ሌላውም ሰው ከልካይ የለውም። ይመጣል። ይሄዳል።» ለነገው ሥራዬ ጥሩ ዜና ነበር።

የካቲት 16 እና 17 ሁለት፣ ግን አጫጭር ቀናት ነበሩ። በእርግጥ አዲሱ «ሌላውም ሰው ከልካይ የለውም። ይሄዳል። ይመጣል» ሲል የነገረኝ ከልቤ አልጠፋም። ቢሆንም ሠፈራ ጣቢያውን በሩቁ መቃኘት፣ ቀስ በቀስ መቅረብና ጉብቶ መመልከት አስፈላጊ ነበር። 14,000 ሠፋሪዎች እንደያዙ የሚገመቱት አረንጓዴ ድንኳኖች በሩቁ ለሚመለከታቸው ረድፍ ጠብቆ የበቀለ ቁጥቋጦ ይመስላሉ። ከእነዚህ ድንኳኖች ውስጥ ለመግባት ጭንቅላት ከጉልበት መታጠፍ አለዚያም መንበርከክ ያስፈልጋል። ከውጭ የቆመው ሕዝብ ሲታይ ድንኳኖች ውስጥ ሰው የቀረ አይመስልም። ድንኳን ውስጥ ሲገባ ደግሞ መረማመጃ ቀርቶ ጠጠር መጣያ ቦታ የለም። ዓይን ተወርውሮ ማየት እስከሚችልበት ርቀት ድረስ ሰዉ አንዱ በአንዱ ላይ ተነባብሮ ተኝቷል። ድንኳን ውስጥ ያሉት፣ ሁሉም ማለት ይቻላል፣ ሕፃናትና ደካማ አረጋውያን ናቸው። ሁኔታው ይህ ነው።


ሰፋሪዎቹ በድንኳን ውስጥ

አዩኝ አላዩኝ ብሉ ጥቂት ፎቶግራፎች ማንሳት ይቻል ይሆናል። ሰዎቹን መራርጦ ተስማሚ ቦታ ይዞ ለመነጋገር ግን ሁኔታው አይፈቅድም። በዚህ ቦታ የሚገኙ ሁሉም ሰፋሪዎች ብቻ ሳይሆኑ «ሠራተኞችም» ይኖራሉ። ስለዚህ ከሰፋሪዎቹ ውስጥ ቀስ ብሉ ሰው ማፍራት፣ በሰው ርዳታ ምሥራቅ ወለጋ ላይ የደረሰባቸውን ችግር መግለጥ የሚችሉ ሰዎችን ማግኘትና አመቺ ቦታ ይዞ ማነጋገር አስፈላጊ ነበር። ይኸ፣ ይኸ ጊዜውን በላው።

ዛሬ ሁኔታዎች ተባብሰው ወይም ተሻሽለው ሊሆን ይችላል። አላውቅም። በወቅቱ ግን ከሠፈራው ጣቢያ በየዕለቱ ሁለትና ሦስት ሬሣ ይወጣ ነበር። የሚሞቱት ሕፃናት ናቸው። ቡሬ እንኳንስ እንግዳ ልታስተናግድበት ለራሷም የምትጠጣው ውሃ የላትም። ለሠፋሪዎቹ ውሃ በቦቴ እየመጣ ሲከፋፈል አይቻለሁ። የሠፈራው ጣቢያ የመፀዳጃ ሁኔታ ለወረርሽኝና ለበሽታ መቀስቀስ በሚያመች ሁኔታ የትም ነው። ያስፈራል። በዚህ ላይ የአማራን ትምክህት ለመዋጋት የቆሙት የክልል ሦስት ባለሥልጣናት ለእነዚህ ከወለጋ ተቀጥተው ጉጃም ለገቡት መከረኞች የሚራራ ልብ ያላቸው አይመስልም። ዘግይተው እየመጡ ለአሉት የወለጋ ተፈናቃዮች ዕርዳታ እንደደረሱ አይሰጥም። «እናንተማ ከብቶቻችሁንና እህላችሁን ስትሸጡ ቆይታችሁ የመጣችሁ ስለሆነ ለእናንተ ዕርዳታ አንሰጥም» እያሉ እንደሚጨክኑባቸው ስደተኞቹ ያስረዳሉ።


ለሰፋሪዎቹ ውሃ ከቦቴ ሲታደል

## የተዋለባቸውን ግፍ ይናገራሉ

እነዚህ ምሥራቅ ወለጋ ላይ ከተፈፀመባቸው ዕልቂት ተርፈው ዛሬ ቡሬ ሠፈራ ጣቢያ የሚገኙት የአማራ ተወላጆች ወደ ወለጋ የሄዱ በተለያየ ጊዜ መሆኑን ይናገራሉ። በአጠቃላይ ግን «በደርግ ዘመንና ከኢሕአዴግ በኋላ» ብሎ በሁለት ጊዜያቶች መከፈል ይቻላል። በእነዚህ በሁለት የተለያዩ ጊዜያቶች ወለጋ የገቡት ገበሬዎች የእርሻ መሬት ያገኙበት ሁኔታም ይለያያል። ይሁን እንጂ ዛሬ በሁሉም ላይ የደረሰው ሰቆቃ አንድና ተመሳሳይ ነው። በመሆኑም በዚያ መከራ ውስጥ ያለፉት ሁሉ ስለደረሰባቸው ችግር የሚናገሩት ከመርሳትና ከማስታወስ ወይም ጥቃቅን የአጋጣሚና የአገላለጽ ልዩነት ካልሆነ በስተቀር፣ የሁሉም ታሪክ አንድ ዓይነት ነው። በዚህ ምክንያት አጠቃላይ ችግሩን በተመለከተ ከአነጋገርኳቸው ብዙ አርሶ አደሮች ውስጥ ሁለቱ ብቻ፣ አንዱ በደርግ ዘመን ሌላው ከኢሕአዴግ በኋላ ወለጋ የገቡ አርሶ አደሮች የተናገሩት ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።

### በርይሁን አያሌው

«አገሬ ወሎ ነው። ወደ ወለጋ የሄድሁት በ1976 ዓ.ም. ነው። በ1976 ዓ.ም. መሬቱ ጫካ ነበር። መንግሥት ግቡ አለን። ገባንበት። ስንገባ ምንም አልከፈልንም። ካርኒ ቆርጠን እንገብር ጀመር። መሬቱ የመንግሥት ነው። በ76 ችግር አልነበረም።

«ችግሩ የመጣ አሁን ነው፤ ኢሕአዴግ ከገባ በኋላ። በድንበር እንካሰሳለን። ስንካሰስ ቀበሌ የእኛን ማመልከቻ ከስር የእነሱን ከላይ ያደርገዋል። ቀበሌ ጨቆነን ብለን ወረዳ ስንሄድ ፖሊስ ጣቢያ እየወሰዱ ያስሩናል። ቀበሌውና ፖሊስ ጣቢያው እስከ ወረዳ ፍርድ ቤት ድረስ <እናንተ ወሎዎች! እናንተ ቋራዎች! እናንተ ጉጃሞች! በእኛ መሬት ማን ተከራካሪና ተሟጋች አደረጋችሁ? የዕለቱን ብቻ ብሉ። እኛ አገር ባፈራችሁት ሀብት ማዘዝ አትችሉም። የዕለቱን እየበላችሁ ተቀመጡ። ከእንግዲህ ወዲያ ማን ያስቀምጣችኋል?> ይሉናል። እኛም <ልጅ ሆነን መጥተን እዚህ አደግን። እዚህ ተወልዶ ያገባ

ሞልቷል። እየተዛመድን ነው። መንግሥት የሰጠን መሬት ስቅቀን ወዴት እንሄዳለን? ደግሞስ በዝዛ ሀብታችን እንዴት እንደዚህ ይሉናል?› እያልን ቆየን። እውነት አልመሰለንም ቆየን።

«ወደኋላ ነገር አመጡ። ስንከራከር ያስሩናል። ገንዘብ እየከፈልን እንወጣለን። አሁን ሌሊት ሌሊት ስርቆት ተጀመረ። የሌሊት ሌባ ድሮም የቆየ ነው ብለን ከብቶቻችንን ስንጠብቅ ፖሊስና ምክር ቤት ከላይ መጥተው መሣሪያ ግዙ አሉን። መሣሪያ ገዝተን ‹አስመዝግቡ› ሲሉን በሕጋዊ መንገድ አስመዘገብን። ከዚያ ‹እናንተ በእኛ አገር መሣሪያ ልትይዙ አይገባችሁም› ብለው፣ ሕግ አስመስለው ገፍፈው እዚያው ለእኛ ጎደኞች ለወረሞዎች አስታጠቋቸው።



ብርይሁን

«ከብቶቻችንን ሌሊት ሌሊት ይሰረቁ ጀመር። ወደኋላ ቀን ቀን መዝረፍ ተጀመረ። ‹ከብታችንን ለምን ትወስዳላችሁ?› ስንል አረኞችን ገደሉብን። ምን እናድርግ እያልን ሳለን እንደገና ‹ተረጋጉ› አሉን። ‹መሣሪያ ግዙና ሀብታችሁን ጠብቁ። ከእንግዲህ ነገር የለም። የንብረ ታችሁ ጌታ ናችሁ› ሲሉን መልሰን መሣሪያ ገዛን። ተእኡኡ አገር፣ የነሱን መሣሪያ ነው የገዛን። ‹አስመዝግቡ› አሉን። አስመዘገብን። አሁንም ሁለተኛ ገፈፉን። ‹ከብቶቻችንን ከተውልን ደግ ነው› ብለን ዝም ብለን ተቀመጥን። ሕጉንም ከላይ እንዳልሆነ አይተነዋል። ‹አቸገፈውናል። ተቸገፈናል› ብለን ተቀመጥን። እንዲያ ተቀምጠን እያለን ባለሥልጣኖች መጥተው ‹እናንተ ከእንግዲህ ያለባችሁ ወደ ክልል ሦስት መግባት ነው። መግቢያችሁ ደረሰ። ሀብትም ከዚህ ይዛችሁ አትሄዱም። ዐመላችሁን አሳምራችሁ ሹለኩ። ካልሸለካችሁ ሕይወታችሁ ይጠፋል› አሉን። መንግሥት እንዲህ ያደርግ አልመሰለንም። አሁን ከብቶቻችንን ቀን ቀን ይዘርፉን ጀመር። ለመከላ ከልም አቅም አጣን። መሣሪያችንን ተገፍፈናል። ከዚያ በኋላ ‹ተነሱ› አሉን። በቃ! የሚገድሉትን ገደሉ። ገደሉ። ገደሉ።

*ፖሊሲው አማራን ማስወጣት ብቻ ሳይሆን አማራ እንዳይገባም ይከለክላል።*

*ባለው የጉሣ ፖሊሲ መሠረት በአሁኑ ጊዜ የአማራውን ተወላጅ እየጨፈጨፉና እያሳደዱ ከወሊጋ ማስወጣት ብቻ ሳይሆን ወደ ወሊጋም እንዳይገባ አገዳ እየተደረገ ነው። ከአንድ ወር በፊት ወሊጋ ይኖሩ ከነበሩ አማራዎች ውስጥ ዘመድ ጠይቀው ለመመለስ ጉጃም መጥተው ነበር። የካቲት 14 ቀን 1993 ወደነቀምት (ወሊጋ) ለመመለስ በሦስት መለስተኛ አውቶቡሶች ተሳፍረው ሄዱ። ኪራም ላይ ሲደርሱ 10 የሚሆኑ የኦሮሞ ፖሊሶች አትሄዱም ብለው መለሷቸው።*

*ይሁን እንጂ ከሦስቱ አውቶቡሶች አንዱ፣ የሠሌዳው ቁጥሩ 3-13316 የሆነውና አቶ ተሻለ ዓለማየሁ በተባለው ሾፌር የሚነዳው በአጋጣሚ አልፎ ሄደ። ሁለቱ የሠሌዳ ቁጥር 3-39522 በአቶ ቴዎድሮስ ዘርዓይ የሚነዳውና አቶ አምሳሉ ወርቅነህ የሚያሽከረከሩት የሠሌዳ ቁጥር 3-13282 አቶቡሶች ሰዎችን እንደ ጫኑ ተመልሰዋል። ቤተሰቦቻቸው ወሊጋ፣ እነሱ ክልል ሦስት።*

«ይህ የሆነው ኅዳር 21 ቀን ነው። ወረዳው በፊት መጥቶ ፈተሸ። ከዚያ ሠራዊት መጣ። ከየት እንደመጣ አናውቅም። የታጠቁ ናቸው። ‹አቤትህ እንዳትቀር› እያሉ ገበሬውን ጨምረው እነሱ ከፊት ከፊት ገበሬው ከኋላ ሆነው ሕዝቡን ጨፈጨፉት። አጠፉት። ከሞት የተረፈውን ወደ እስር ቤት ወሰዱት። ከዚያ እየሸለከን ሀሮ ከሚባል የስመሮ ቦታ ላይ ተሰበሰብን። ዳኞች ናቸው የተባሉ መጡና ሰበሰቡን። ያልተነኩትን ቀበሌዎች እየደበደቡ ከእኛ ዘንድ አመጧቸው። እዚያ ታከተን ቆየን። ሕጣናት በረሃብ እየተሰቃዩ ሞቱ። ደካሞች ሞቱ። ትንሽ አቅም ያለው እየሸለከ ከዚህ ደረስን።

«ከ15 ያላነሱ የቀንድ ከብቶች፣ 12 ፍየሎች፣ አንድ አህያ ነበሩኝ። እኩሌታው እዚያው ቀረ። እኩሌታው ዐባይን እስከንሻገር ድረስ ዝርፊያው አላቆመም ነበርና ወሰዷቸው። እህሉ ሁሉ እዚያው ቀረ። መሣሪያ ነበረኝ። ወሰዱት። ስድስት ልጆች አሉኝ። ሁሉንም ይገፍ መጥቻለሁ።»

## ዓለሙ መኩንን

«ከጉንደር በ1990 ነው ወደ ወለጋ የሄድሁ። መርጃ ጂረኛ ቀበሌ እናር ነበር። መንግሥት ‹መሬት ባለቤት ሠርተህ ብላ› የሚል መስሎን ነበር። መጀመሪያ ስንደርስ ለመመዝገቢያ ሁለትም ሦስት መቶ የከፈልን አለን። ያን ካስከፈሉን በኋላ ለባለመሬት ያስተላልፉናል። ባለመሬቱ መሬት ሰጥቼሃለሁ ይልና እንደ መሬቱ መጠን ሁለትም፣ ሦስትም ሺ ብር ይቀበለናል። ከዚያ መሬት ይዘን እናርሳለን። ቀይም ብለው የሄዱት ተመርተናል ይላሉ።

«መሬት ከሰጡን በኋላ ገንዘቡ ሲያልቅ ለመክሰስ ይነሳሉ። ከገበሬ ማኅበር የክስ ደብዳቤ ያመጣሉ። አክብረን መልስ ይዘን እንቀርባለን። ‹አልተስተካከለም› ብሉ ኪሣራ ይቆርጥብናል። የምና ቀርበው መልስ አይታይም። እንታሰራለን። ‹ዋስ ጥሩ እንባላለን።› አማራ መሬት ስለሌለው ዋስ አይሆንም። ሌሎችን በሺ ብር እየገዛን ዋስ እንጠራለን። ‹ከሣምንት በኋላ ቅረቡ› ይሉናል። እንቀርባለን። ዋሳችን ‹ዋስትናየን አውርጃለሁ ይላል›፣ ሺ ብር የከፈልነው ዋስ። ታሰሩ እንባላለን። ሌላ ሺ ብር ከፍለን ዋስ እንጠራለን።



ዓለሙ መኩንን

«ብዙ ስንማረር፣ ስንማረር በኋላ ስርቆት ተጀመረ። ስርቆት ይጣላል እንጂ ዘረፋ ነው። ከግንቦት እስከ ሐምሌ 1992 ዘረፋው ቀጥሏል። ሐምሌ 7 ቀን በሬ ተሰረ ቀና እሬ ተባለ። ተሰበሰብን። ‹ምን እናድርግ? ምን ይሻላል?› ተባባ ልን። ይህን ሁሉ የሚሠራን የገበሬ ማኅበሩ ሊቀመንበር ወይም ፀሐ ፊው ነው። ታጣቂዎች ናቸው። በሬአችንን እናስመልስ ብለን ከፀሐፊው ዘንድ ሄድን። ፀሐፊው ደረጃ መለስ ይባላል። እየሄድን ሳለ የአየለ አዱኛ ቤት ተዘረፈ። ‹ኡ! ኡ!› ተባለ። የሄድነውም ተመልሰን መጣን። ከላይና ከታች ያለው ሰው ተሰባሰበ። እንደ አጋጣሚ ተኩስ ተተኩስና ሁለት ሰው ቆሰለ። ይህ የተፈጸመው ሐምሌ 8 ቀን ነበር። ሐምሌ 10 ቀን ‹የበላይ አካል ነን› ብለው መጡ። ይህን ሁሉ የሚሠራን የበላይ አካል እየተሰኘ ነው። ይህን የሠራን የመንግሥት አካል ነው። ገበሬው አይደለም። ልንጮኸለትም አቅቶናል። ‹እኛ እንግዲህ ይህን መንግሥት ብለን እንዴት መቀመጥ እንችላለን? ዳኝነትስ እንዴት አለ ማለት ይቻላል?› ስንባባል ሐምሌ 19 ቀን የበላይ አካል ተወካዮች መጡ ተባለ። ትክክለኛ ዳኞች ናቸው ሲባል ጊዜ ገበሬው ተሰበሰበ። ከክፍለ ሀገር፣ ከፖሊስ፣ ከገበሬ ማኅበር የመጡ ናቸው።

«የወረሞ ገበሬዎች ሣር አጨዱ ደን ጨፈጨፉ ይሏችኋል› አሉን። ‹መሬት ሰጡን። እረሱት፣ እንጨቱን ቁረጡት፣ ሣሩን እጨዱት አሉን። አረስን፣ አጨድን፣ ቆረጥን፣ ይሽ ምን ጥፋት ሆኖ ይታያል?›

አልን:: <የእኛ ጥፋት ነው ብላችሁ እመኑ> ተባልን:: <እረሱ ባልተባልን እንጂ ይህ እንዴት አድርጐ ጥፋት ይሆንብናል> ብለን ብዙ ተጨቃጨቅን:: <አሁን እናንተ ጥፋታችሁን በትክክል ካላመናችሁ፣ ጥፋተኛ ነን ካላላችሁ የወረሞ ክልል እናንተን ሊቀበላችሁ አይችልም> አሉን:: እንዲህ ከሆነማ ምን እናደርጋለን? <ብደለኛ በደለኛ ወታደር በደለኛ፣ ግን ቢሆን ባላገር ይካስ> ከትባለ፣ ይህ በደል ከእኛ ከሆነ ሳሩንም አጭደነዋል እንጨቱንም ቆርጠነዋል:: ያው ለእንጀራ ብለን ነው አልናቸው:: ይህ ጥፋት ነው ከተባለ ተቀብለነዋል አልን:: ወረሞዎችም ጥፋታችን ብለው አመኑ::

«ከእንግዲህ ተስማምታችሁ ኑሩ ተብለን ሽማግሌዎች ከወረሞም ከአማራም ተመረጡ:: የጠፋው ሁሉ በቅንጅት እንዲመለስ ተባለ:: <አገሪቱ ኢትዮጵያ የሁሉም የጋራ ናት:: የወረሞም የአማራም ብቻ አይደለችም:: አገሩ የጋራችን ነው:: እኛም የሁላችሁም ዳኞች ነን> አሉን:: ሽማግሌዎቹ ሲደክሙ ሪፖርት ሲተላለፍ ቆየ:: እኛ ቋንቋውን አናውቀውም:: ይህ ሲሆን ብዙ ቆየ:: እሱስ ሲመክሩ ቆይተዋል::

«ኅዳር 21 ቀን የማርያም፣ ዳቡክ ማርያም በዓል ነበረ፣ ወረዳው <ተሰብሰቡ> አለና ጠራ:: ለበዓሉ የመጣው ሰው ሁሉ አለ:: ወረዳውን እኔም በአካል አውቀዋለሁ:: አሰፋ ፈይሳ ይባላል:: ሌሊት ከምሽቱ 5 ሰዓት ገብቶ ነው ያደረ:: የአካባቢው ሰው ይሰበሰብ ጀመር:: ከጠዋቱ አንድ ሰዓት አካባቢ ይሆናል:: መትረየስ ጠምዷል:: ሰው ሲሰበሰብለት በመትረየስ አጨደው:: ዓመት በዓልም ስለነበረ የተሰበሰበው ሰው ብዙ ነበር:: አብረውት የነበሩ ሁሉ ተኩስ ከፈቱ:: ተኩስ ሲከፈት ሰው በየአቅጣጫው ሮጠ:: ላውንቸር አለ:: የማላውቀው የመሣሪያ ድምፅም ነበረ:: ሲተኩሱ ሲገድሉ ውለው ሄዱ:: ኅዳር 21 ቀን ጥይቱ ሁሉ የሚተኮስ ከእነሱ ነበር:: ግን ከዚያም ወገን ሰው ሞቷል አሉ::

«ኅዳር 25 ቀን እንደገና ጦር ተጭኖ መጣ:: ሠራዊት ነው:: መትረየስ፣ ክላሽ፣ ላውንቸር ታጥቋል:: ቁጥሩ አይታወቅም በቅጠሉ ቁጥር ነው:: ብዛቱ ይነገር ቢባል 500 እና 600 ይሆናል:: ሰውን ይገድል፣ ቤቱን ያቃጥል ጀመረ:: የአካባቢውን ሰው እየያዘ ገደለ:: እኔ እንኳን የማውቀው ብዙ ሰው ሞተ:: ከኅዳር ማርያም ጀምሮ ያለቀውን ሰው እግዜር ይቁጠረው:: እኔ እንኳን የማልረሳቸው ቁጥር የላቸውም::

ዝብያው ሙሉነህ፣ ፈጠነ ገብሬ፣ ኢያል አዱኛ፣ ጋሻው እውነቱ፣ ጋሻዬ ጌቴ፣ ይበልጣ መንግሥቱ፣ ይበልጣ ድረስ፣ አዘዘ ይበልጣ፣ ይግዛው ታምራት፣ አሻግሬ ገበየሁ፣ መልካሙ አሻግሬ፣ ተሾመ ቸኮል፣ ደምሴ ይመር፣ ወርቁ ገበየሁ፣ አስረግደው ውቡ፣ ተስፋዬ ዓለማየሁ፣ ሰጤ ወርቅዬ፣ መልካሙ ውባለም፣ ውቡ ሞንሚኔ፣ ምሕረት እውነቱ፣ ቢራራ ታደሰ፣ ደስታው አብተው፣ አባ በላይ ዋለ፣... አረ ስንቱ! ያለቀው ቁጥር የለውም:: እኔ ድሮ የማውቀው በኃይለሥላሴም ደርሻለሁ፣ በደርግም አልፌአለሁ ቤቱን ከፍቶ የሚቆይ አማና ሰው አይደበደብም:: አይገደልም:: ሰላም ነው ብለው ከቤታቸው የተቀመጡትን ሰዎች <ከክልል ሦስት ነው የመጣን:: ልናረጋጋችሁ መጣን:: ከባሕር ዳር ነው የመጣን> እያሉ ቤቱን ከፍቶ ሲያገኙት ያው መግደል ነው:: ገደሉት:: ቤቱን በእሳት፣ ክምሩን በእሳት፣ አነደዱት:: ሰውን በጥይት ፈጁት::» የሞተው ቁጥር የለውም:: ሺ ነው::

እስከ ኅዳር 27 እና 28 ድረስ ዕልቂት ነበር:: ይተኩሳሉ:: ይገድላሉ:: የተቀመጠውን በዱላ የሚሮጠውን በጥይት ይሉታል:: ልጅም፣ ሕጣንም፣ ሴትም ዱላ ያበዛበት ፈቀቅ ሲል በጥይት ነው:: ወንጀሉ ይኸ ነው አይባልም:: ጥያቄም የለበትም:: <ከመስመር ወዲህ ያለውን አማራ በጠቅላላ አጥፉ ነው የተባልነው> አሉ:: ወደ ድሬ፣ ወደ ሀሮ የሚያወጣ መንገድ አለ:: ከዚያ ወደዚህ ሰባት ገበሬ ማኅበሮች ነን:: እነዚያ በሙሉ <እንዲጠፉ ታዝዘናል> ይሉ ነበር:: <ትዛዝ ነው፤ አባቴን ባገኝም አልምርም:: እናቴን ባገኝም አልምርም:: ሁላችሁንም እናጠፋችኋለን> አሉ:: አጠፉን:: የተቀበረም የለም:: ያለቀሰም የለ:: ንብረትም እዚያው ከሰለ:: ሕይወትም እዚያው አለቀ::» ■

አያል አቾኔ ከሞጣ አውራጃ፣ ከጉምደወይን በ1988 ከባሏ ከይታየው መሥፍን ጋር ወደ ወሊጋ ሄደች:: ኅዳር 28 ቀን 1993 በታጣቂ ቤታቸው ተቃጠለ:: መሥፍን ጥጆችን እየተቃጠለ ካለው ቤት ውስጥ ለማውጣት ሲሄድ በጥይት ጣሉት:: አሁን አያል አቾኔ አራት ልጆች ይዛ ቡሬ ሠፈራ ጣቢያ ትገኛለች::



አሰፋሽ ገዚ ከባሏ ቀኜ ግዛው ሦስት ልጆች ወልዳለች:: ቀኜ ግዛው ኅዳር 27 ቀን በጥይት ተገደለባት:: ሦስት ልጆች ይዛ ሜዳ ላይ ቀረች::



## ከዕልቂቱ አስከፊ ገጽታ በከፊል

«ጌጣ ጌጡን አይተው አንቀልባውን ለመውሰድ በኃይል ጉትተው ሲፈቱት የሁለት ዓመት ሕፃን ከእናቱ ጀርባ ከሚነደው ቤት ደጃፍ ላይ ወድቆ በእሳት ተቃጥሎ ሞተ::»

«መልካሙ ውባለም የተባለውን ገድለው ምላሱን አውጥተው ወሰዱት::»

«አስረግደው ውቡ የተባለውን በጥይት ገድለው አንካሴ አንገቱ ላይ፣ ወገቡ ላይ እግሩ ላይ ቸክለውበት ሄዱ::»

«አንድ ሴት ሦስት ልጆቿን አስከትላ ስትሸሽ ወንዝ ላይ ስትደርስ በጥይት ገደሏት:: ሦስቱ ልጆች በርረው ወንዝ ውስጥ ገቡና እዚያው ሞተው ቀሩ::»

«አባ በላይ ዋለ የተባሉትን ዓይነ ሥውር ገደሏቸው:: አማራ አማራ ነው ብለው ብልታቸውን ቆረጡት::»

«መልካሙ ውባለምን አርደው ገደሉትና ምላሱን አውጥተው ወሰዱት»